# ለድል ተሰማራ!!

ተገለህ ስትጣል እንደ ዱር አውሬ፡
ውጭ ሀገር ተቀምጦ ምን ሊፈይድ ወሬ፡
ወገን ሲጨፈጨፉ በነጋ በጠባ፡
በገዥዎች ትእዛዝ በካዲዎች ደባ፡
በስርቤት ታጉሮ በሳት ሲጠበስ፡
በውነት ፉጡራነን ለወገን ምን ደርስ?
በሳይበሩ አለም የምንኖር በአፉ፡
ዘራችን በጥይት እንደ ቅጠል ሲርግፉ፡
ሰው ሆነን ለመኖር ምንድን ነው ትርጉሙ፡
በተግባር የሌለን ሁሌ ማጉረምረሙ፡
የቡና ላይ ወሬን እርም ብለን ተፉተን፡
ለድል እንነሳ እንታገል ተግተን፡
ሁሌ ከምንኖር እንባ እያነባን፡
ለድል እንነሳ ባንድ ላይ ሆነን፡
የትላንቱ ህፃን ሞትን  ሲደፉር፡
መሆናችንን አውቀን ከሞት የማንቀር፡
ዝም ብለን ከምናልፉ ለወገን ሳንሰራ፡
ሀሜት አስወግድህ ለድል ተሰማራ፡
ነፃነት አይመጣም ቁጭ ብሎ በወሬ፡
መጣላችን ያብቃ ተገለን እንዳውሬ፡
ብዙሀን ሆነን ሲገሉን አናሳ፡
ይሄ ወኔ ሰቶህ ለድል ካልተነሳ፡
ነዋሪ መሆን ቀርቶ ከሆን በቁም እሬሳ፡
መገደል ካልቆመ እንደዱር እንሰሳ፡
በወሬ ነጻነት ይቅር አይነሳ፡;

ስለዝህ ሰው ሆነን እንደ ሰው ልንኖር፡
ሁሌ በገዥዎች እንዳንባረር፡
ነጻነት በደም ነው በወሬ የማይመጣ;
እስከ መጨረሻው እንዲያበቃ ጣጣ፡
ለድል እንነሳ ከነገር ሰንጠቃ፡
ዘወትረ መሰደድ ከቶ እንዲያበቃ፡
ሀብት ያለው በሀብቱ እውቀት ያለው በውቅት፡
ሀገርን ተባብረን ልንገነባ በውነት፡
ኦሮሞ እንዳያልቅ ካልቆምንለት ዘብ፡
በውጭ አለም ኖረን  ሁሌ በጥጋብ፡
ሰው መሆን  ያንሰናል አይደለን ሙሉ ሰው፡
እንደድንች ሁሌ ማንም የሚጠብሰው፡
የባርነት ቀንበር አሽቀንጥረን ጥለን፡
ለድል እንነሳ ባድነት አብረን፡
እንዲህ ተበታትነን አይመጣም ነጻነት፡
ለድል እንታጠቅ አንድ ሆነን በህብረት፡
ሁል ግዜ ድርጅት ከምንፈበርክ፡
ቀጥ ብሎ የማይሄድ እንጂ በንብርክክ፡
እንደ ደመኛ ሰው ከመኖር ተኮራርፈን፡
ይቅር ተባብለን ባንድነት ተባብረን፡
እንኮን ለራሳችን ለሰው እንተርፋለን፡
የወገን ደም መላሽ ወገን ስለሆን፡
ባለን እንሰለፉ እንደምስሰ ወያኔን!!
ድል ለኦሮሞ ህዝብ!!
Gadaan Gadaa Bilisummaati!
Meseret Tulu